DC HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# ምልክት የማያሳዩ ሰዎች የትምህርት ቤት የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ የፍቃድ ቅጽ

**የDC Health እና የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ልጅዎን ለCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ኢንፌክሽን ለማስመርመር የእርስዎን ፍቃድ ለማግኘት** እና የተሰበሰበውን ዳታ አግባብ ላላቸው ባለስልጣናት ለማጋራት ይህን ቅጽ እየተጠቀመ ነው። ምልክቶች፣ ምርመራ፣ እና የኮሮናቫይረስ ምላሽ ላይ ተጨማሪ መረጃ በ cdc.gov/coronavirus መገኘት ይችላል። የኮሮናቫይረስ ምልክቶች እና የኮሎምቢያ ግዛት ምላሽን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ በ www.coronavirus.dc.gov ማግኘት ይችላል። ደህንነቱ የተጠበቀ በአካል ትምህርት COVID-19/ኮሮናቫይረስ ለመለየት እና ስርጭቱን ለመከላከል ትትርናን ይጠይቃል። ይህ ምርመራ ነጻ(ክፍያ የሌለው) እና በፍቃደኝነት ነው።

**እንዴት መምረጥ እችላለሁ?** ልጅዎ እንዲመረመር ይህን የፍቃድ ወረቀት ሙሉ በሙሉ መሙላት እና መመለስ አለብዎ። ይህ የፍቃድ ወረቀት የልጅዎ ትምህርት ቤት ውስጥ ይቀመጣል። ልጅዎ በተመረመረ በእያንዳንዱ ጊዜ ለመርማሪው ቡድን ይቀርባል። ይህ የሚደረገው ልጆች ያለ ወላጅ/ሞግዚት ፍቃድ እንዳይመረመሩ ለመከላከል ነው። ይህ የፍቃድ ቅጽ ከተፈረመበት ቀን አንስቶ **ለ90 ቀናት** የጸና ነው።

**እንዴት አለመምረጥ እችላለሁ?** ልጅዎ ለCOVID-19/ኮሮናቫይረስ እንዲመረመር እንደማይፈልጉ የሚገልጽ የጽሁፍ ደብዳቤ በመላክ በማንኛውም ጊዜ ፍቃድዎን መሻር ይችላሉ።

**ምርመራው ምንድነው?**
***ከተስማሙ፣*** ልጅዎ ለ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ቫይረስ ነፃ የህክምና ምርመራ ያገኛሉ። **የተያያዙ ሰነዶች ጥቅም ላይ መዋል ስለሚችሉ ምርመራዎች ተጨማሪ መረጃን ያቀርባሉ።** ለምርመራ ናሙናዎችን ለመውሰድ ከQ-Tip ጋር የሚመሳሰል፣ትንሽ የመጥረጊያ መሳሪያን፣ የአፍንጫ ፊት ለፊት በኩል ሁለቱም የአፍንጫ ቀዳዳዎች ዉስጥ መከተትን ይጠይቃል። ይህ ምርመራ በግዛቱ የህዝብ የምርመራ ጣቢያዎች የሚደረገው ምርመራ ጋር ተመሳሳይ ነው። በCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ምክንያት በበሽታው የመያዝ እድል አይኖርም።

**ስለ ምርመራው ዉጤቶች እንዴት ማወቅ እችላለሁ?**
የምርመራ ውጤቶቹ ለእርስዎ በቀጥታ ይላካሉ። በሚሰጡት የኢሜይል አድራሻ ውጤቶቹ በኢሜይል ይደርስዎታል። ይህ ፈጣን ምርምራ አይደለም። በተለምዶ ውጤቱ በ5 ቀናት ውስጥ ይደርሳል። የምርመራ ውጤቱን በተመለከተ የኩሬቲቭ ላብራቶሪ የምርመራ ማእከል ጋር በ**1-888-702-9042 በመደወል መከታተል ይችላሉ።**

**የልጄን የምርመራ ዉጤቶችን ሲደርሰኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**
የልጅዎ የምርመራ ዉጤት ፖዘቲቭ ከሆነ፣ልጅዎ ቫይረሱአለበት እና ማሰራጨት ይችላል ማለት ስለሆነ፣የምርመራ ዉጤቶችን ለመገምገም እና ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ለመነጋገር እባክዎ ዉዲያዉኑ የልጅዎን የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ያግኙ። ልጅዎን ቤት ዉስጥ ማቆየት አለብዎ እና ወደ ትምህርት ቤት ለማስመለስ የጤና እና የትምህርት ቤት መመሪያዎችን ይከተሉ። ልጅዎ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራው ፖዘቲቭ ከሆነ ከዲሲ የጤና ዝኪኪ መለያ የስልክ ጥሪ ይደርስዎታል። የልጅዎ የምርመራ ዉጤት *ኔገቲቭ ከሆነ፣* ይህ ማለት ቫይረሱ ልጅዎ ዉስጥ አልታየም ማለት ነው። በበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማእከላት (CDC) የተመከሩ ንጽህናን እና የማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ ልምምዶችን ይቀጥሉ። ልጅዎ ምልክቶችን ካሳየ/ች፣ ለ ልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ መደወል አለብዎት፣ የምርመራ ውጤቶቹ ምንም ቢሆኑም። ለዲስትሪክቱ ኗሪዎች የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ህክምና ነጻ ነው።

***ዳታ እና ሪፖርቲንግ***
ከዚህ ቅጽ የሚገኙ ዳታ እና የምርመራው ዉጤቶች እንደ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶች ይሰበሰባሉ እና ለሚመለከታቸው የትምህርት ቤትና የጤና ባለስልጣናት ሊጋሩ ይችላሉ። ልጅዎ የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ውጤቱ ፖዘቲቭ ከሆነ ማንነቱ ሊሆን ለሌሎች ይፋ አይደረግም።

| የግንኙነት መረጃ \| በ ቤተሰብ/ሞግዚት/ተማሪ ( 18 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ) ይሞላል። | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የተማሪ የአያት ስም፥ | የተማሪ የመጠሪያ ስም፥ | | የትውልድ ቀን፥ | |
| የትምህርት ቤት ስም፣ | | | ዋርድ፥ | |
| የቤት አድራሻ፥ | አፐት/አፓርትመንት፥ | ከተማ፥ | አገር፣ | ዚፐ፣ |
| የወላጅ/ የሞግዚት ስም፥ | ስልክ ቁጥር፣ | ኢሜይል፣ | | |
| በድንገተኛ ጊዜ የሚጠራ ሰው ስም፥ | | በድንገተኛ ጊዜ የሚጠራ ሰው ስልክ፥ | | |

ከዚህ በታች በመፈረም፣ ከዚህ በታች ያሉትን አረጋግጣለሁ፥

- ይህንን ቅጽ በነፃነት እና በፍቃደኝነት ፈርሜያለሁ፣ እና ከላይ ለተገለጸው ልጅ ዉሳኔዎችን ለማድረግ ሕጋዊ ስልጣን አለኝ።
- ልጄ ለCOVID-19 እንዲመረመር ፍቃዴን ሰጥቻለሁ።
- እኔ በጽሁፍ ለልጄ ትምህርት ቤት የሚመለከተው ሀላፊ ፍቃዴን እንደሻርኩ ካላስታወቅኩ በስተቀር ፍቃዴ በዚህ ቅጽ ላይ ከተገለጸው ቀን ጀምሮ ለ90 ቀናት የጸና ነው።
- የልጄ የምርመራ ዉጤቶች እና ሌሎች መረጃዎች በህግ እንደተፈቀደው ይፋ ሊደረጉ እንደሚችሉ እረዳለሁ።
- እኔ እድሜየ 18 ወይም ከዚያ በላይ ወይም በሌላ ሁኔታ ለራሴ ጤንነት ፍቃድ ለመስጠት በህግ የምችል ተማሪ ከሆንኩ፣"የኔ ልጅ" የሚለው ማጣቀሻ እኔን የሚመለከት ነው እና እራሴን ወክየ በዚህ ቅጽ ላይ ልፈርም እችላለሁ።
- ዲስትሪክቱ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ሰራተኞቹ እና ኤጀንቶቹ ለድርጊቶች ወይም ግድፈቶች፣ የወንጀል ድርጊቶች፣ የታሰበበት ጥፋቶች፣ ከባድ ቸልተኝነት፣ ወይም ሆን ተብሎ መጥፎ ምግባር ካልሆነ በስተቀር፣ ከሲቪል ተጠያቂነት ነፃ እንደሚሆኑ እረዳለሁ እንዲሁም እስማማለሁ።
- ዲስትሪክቱ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ሰራተኞቹ እና ኤጀንቶቹ ከካምፓስ ላይ ክትትል የተነሳ የተለየ ተማሪ በቫይረስ ለመያዙ ተጠያቂ ተደርገው ሊወሰዱ እንደማይችሉ እረዳለሁ።

የፍቃድ ፊርማ፣

የቤተሰብ/ሞግዚት/ተማሪ (18 ዓመት ዕድሜ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ) ፊርማ

**ቀን** (ወወ/ቀቀ/ዓዓዓዓ)

| ለቢሮ ሥራ ብቻ \| በትምህርት ቤት ሬጅስትራር እና የትምህርት ቤት ነርስ የተቀበለ የስምምነት ቅጽ | | |
|---|---|---|
| የነርስ ስም፥ | ፊርማ፥ | ቀን፥ |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የDCPS ትምህርት ቤቶች ምልክት የማያሳዩ ሰዎች የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ፣ መረጃ ለቤተሰቦች፣ ሞግዚቶች፣ እና ተማሪዎች

ምልክት የማያሳዩ ሰዎች የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ የሚጠቅመው ለወላጆች ስለ ልጃቸው የትምህርት ቤት አካባቢ መረጃ ለመስጠት ነው። መደበኛ ምርመራ ማድረግ ትምህርት ቤቱ በአካል የመማር ሂደቱን ለማከናወን ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ወላጆች እና ተማሪዎች ሊያረጋግጥላቸው ይችላል።

- ምርመራ የሚሰጠው የተሞላ የስምምነት ቅጽ ላላቸው ተማሪዎች ብቻ ነው።
- ምልክት ለማያሳዩ ምርመራ የሚደረገው በአፍንጫ ስዋብ(የአፍንጫ ውስጥ መጥረግ)ነው። አብዛኛውን ጊዜ ውጤት የሚደርሰው በ5 ቀን ውስጥ ነው። ዉጤቶቹ ለተማሪው ተንከባካቢ ይገለጻል።
- የልጅዎ ምርመራ ዉጤቶች *ፖዘቲቭ* ከሆኑ፣ የምርመራ ዉጤቶችን ለመገምገም እና ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ለመወያየት እባክዎ ወዲያውኑ የልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ያግኙ። ልጅዎን ቤት ዉስጥ ማቆየት አለብዎ እና ወደ ትምህርት ቤት ለማስመለስ የጤና እና የትምህርት ቤት መመሪያዎችን ይከተሉ።
- የልጅዎ የምርመራ ዉጤቶች ኔገቲቭ ከሆኑ፣ ይህ ማለት ቫይረሱ በልጅዎ ናሙና ዉስጥ አልታየም ማለት ነው። በበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማእከላት (CDC) የተመከሩ ንጽህናን እና የማህበራዊ ርቀትን መጠበቅ ልምምዶችን ይቀጥሉ። ልጅዎ ምልክቶችን ካሳየ/ች፣ ለ ልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ መደወል አለብዎት፣ የምርመራ ውጤቶቹ ምንም ቢሆኑም።
- የምርመራ ውጤቶቹ እንዳስፈላጊነቱ ከትምህርት ቤቱ፣ DC ጤና፣ ወይም ሌሎች የአካባቢው እና የፌዴራል የህዝብ ጤና ባለስልጣናት ጋር ሊጋሩ ይችላሉ።
- በቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ሕግ (FERPA) እና የአካባቢው ግላዊነት ጥበቃዎች መሰረት፣ ተማሪው/ዋን በግል ሊለይ የሚያስችል መረጃ ለህዝብ ይፋ አይደረግም። ሁሉም መረጃ በምስጢር ተይዞ ይቆያል።

CDC በ COVID-19/ኮሮናቫይረስ የተያዘ ማንኛዉም ሰው ምልክቶችን ካየ በኋላ፣ በምልክቶቹ ክብደት መሰረት፣ ለ10 እስከ 14 ቀናት ኳራንታይን ዉስጥ መቆየት እንዳለበት ይመክራል።

አንድ ግለሰብ በCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ፖዘቲቭ ሆኖ ከተገኘ ሊተገብረው ስለሚገባ መመሪያ ተጨማሪ መረጃ በ coronavirus.dc.gov/healthguidance ሊገኝ ይችላል።

ስለበሽታው እና የራስዎን እና የቤተሰብዎን ደህንነት እንዴት ጠብቀው መቆየት እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የCDC ኮሮናቫይረስ ድህረገጽን በ www.cdc.gov/coronavirus ይጎብኙ።

ወረርሽኙን ለመከላከል ዲስትሪክቱ እየወሰደ ያለውን እርምጃ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የDC የኮሮናቫይረስ ድህረገጽን በ www.coronavirus.dc.gov ይጎብኙ።

የትምህርት ቤትዎ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምላሽ መስጫ ጥረቶችን በተመለከተ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የትምህርት ቤቱን አስተዳደር እና/ወይም የትምህርት ቤቱን የሬጅስትራር ቢሮን ያግኙ።

**የኮሮናቫይረስ ምልክቶች**

- 100.4 F (38 C) ድግሪ ፋራንሃይት ወይም ከዚያ በላይ የሰውነት ሙቀት
- ብርድ ብርድ ማለት
- ማሳል
- የትንፋሽ እጥረት ወይም ለመተንፈስ መቸገር
- ድካም
- የጡንቻ ወይም የአካል ህመም
- አዲስ የጣዕም ወይም የማሽተት ችሎታ ማጣት
- የጉሮሮ ህመም
- መታፈን ወይም የአፍንጫ ፍሳሽ/ንፍጥ
- ማቅለሽለሽ ወይም ማስታወክ
- ተቅማጥ
- በአጠቃላይ የጤንነት ማጣት ስሜት

ልጅዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ከሌላቸው፣እባክዎ አቅራቢ ለማግኘት የDC ሕፃናት ክትባት ቦታዎችን ይጎብኙ። እነሱ በ dchealth.dc.gov/service/immunization ሊገኙ ይችላሉ።